# ጠመንጃን በጠመንጃ የሚል የትግል ስልት ዘመኑን አይመጥንም ::

ኢህአዴግ በትረ-ስልጣኑን ከያዘ እንሆ 23ኛ ዓመቱን ሊድፍን በጣት የሚቆጠሩ ቀናቶች ቀርተውታል፡፡በዚህ የስልጣን ዘመኑ እሱን ለመታገል የተደራጀን የፖለቲካ ኃይሎች በነዚህ ሁሉ ዓመታት በትግል ስልት ዙሪያ ሦስት ዓይነት አቋም እያራመድን እንገኛለን፡፡

ኢህአዴግን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አልገነባም፤ዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶችን አላከበረም፤ሕገ-መንግስቱ ውስጥ ለህዝብ የማይጠቅሙ አንቀጾችን በምርጫ አሸንፈን ለሕዝብ እንዲጠቅሙ ለምናደርገው ትግል እንቅፋት ፈጣሪ ነው፤በሚል ወደ ሰላማዊ የትግል ጎራ በመቀላቀል ሃሳብን በነፃነት የመግለፅና የመሰብሰብ መብት በመጠቀም ከምርጫ ቦርድ ህጋዊ ሰርተፍኬት ወስደናል፡፡አሁን የምርጫ ቦርድ ባወጣው መረጃ ከ70 በላይ ፓርቲዎች በሰላማዊ ትግሉ ጎራ ተሳታፊ ሆነናል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ በስልጣን ላይ ያለው ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ አንባገነን ነው፤ የፀጥታ ተቋማቱን ተጠቅሞ ይገድላል፤ ያስራል፤ ያፍናል፤ ዴሞክራሲ ሥርዓት አስፍኛለሁ የሚለው ለይስሙላ ነው፣ የመደራጀት መብትም የለም፤የተደራጁ ኃይሎች ቢኖሩም ይታፈናሉ፤ በመሆኑም በጠመንጃ የወጣ ኃያል የሚወርደው በጠመንጃ ብቻ ነው በማለት ገዢው ፓርቲ ሊለወጥ የሚችለው በትጥቅ ትግል ብቻ ነው በሚል መርህ በመስኩ ተሰማርተዋል፡፡

ሌላው በመሪዎቹ በእነ ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ግልፅ ማብራሪያ ሲሰጥ ያልሰማነው ግንቦት 7 እከተለዋለሁ የሚለው የትግል ስልት ሲሆን ይህም የከተማ ውስጥ አመፅን፣ ብጥብጥን እና በሌላ መልኩ የጦር መሳሪያ ትግልን በመቀላቀል ሁለ ገብ ትግልን አካሂዳለው የሚለው የትግል ስልት ነው፡፡

ይሄ ስልት ከትጥቅ ትግል የሚለየው ጥፋቱን ከተማው ውስጥ ማስገባቱ ስለሆነ በአጥፊነቱ ተመሳሳይ ነው፤ ስለዚህ በሰላማዊና በትጥቅ ትግል ዙሪያ ላይ ብቻ አተኩሬ ሃሳቤን ላስቀምጥ:: ነዚህን ከላይ ያየናቸውን የትግል ስልት በአንድ ሀገር ላይ ለመጠቀምና ላለመጠቀም የሚያስችሉ ሁኔ ች ምንድን ናቸው? በሀገራችን ተግባራዊ ቢደረግ አዋጪ የሚሆነውና ጠቃሚው የትግል ስልት የትኛው ነው?

ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ፤ ሠላማዊ ሰልፍ የማድረግ፤ የመሰብሰብ ና የመደራጀት በአጠቃላይ የሰው ልጅ ሰብአዊና ደሞክራሲያዊ መብቶች ጭራሽ ህገ- ወጥ ናቸው ተብሎ የብዙሀን ፓርቲ አሰራር ህጋዊ ውቅና ባላገኘ በት ሀገር በሠላማዊ መንገድ ተደራጅቶ መ ገል ስለማይቻል ብቸኛው አማራጭ የአመጽና የትጥቅ ትግል ማድረግ ነው:: ይህንን በህጋዊ መንገድ ተደራጅቶ መ ገልን ለከለከለ መንግስትም የአመጽንና የትጥቅ ትግልን ህገ- ወጥ ነው ብሎ ማውገዝም አራዶች ንደሚሉት ቅንድብ የሌለው መንግስት ያሰኘዋል:: የማያፍር ንደማለት ነው:: በውጭም ሆኖ ለሚከ ተል ማንኛውም ወገንም ይህንን አማራጭ የወሰዱትን ወገኖች ምክንያ ዊና ፍትሀዊ ናቸው ንዲባሉ ያደርጋቸዋል::

በዚሁ ተቃራኒ ደግሞ ዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶች በህገ- መንግስት ደረጃ ውቅና ባገኙበት ሁኔ ከላይ የጠቀስኩት ወሳኝ የሆኑ የሰው ልጅ መብቶች በተግባር ወይም ከወረቀት አልፎ መሬት ላይ ሲወርዱ ተፈፃሚነቱ ችግር ያለበት ቢሆንም ንኳን በዚያ ሀገር ላይ የአመፅንና የትጥቅ ትግልን ተግባራዊ ማድረግ በህግ ማስጠየቁ የማይቀር ነው:: በነዚህ አገሮች ላይ ተቀባይነት ያለው የትግል ስልት ሠላማዊ የትግል ስልት ነው:: የትግሉም ቀዳሚ ጉዳይ የሚሆነው ህገ- መንግስቱ ላይ የሰፈረውን ግን ተግባራዊ ያልተደረገውን ተግባር ላይ ንዲውል ለመከወን የፖለቲካውን ሜዳ ምቹ ማድረግ ነው:: ይኼን ትግል በተጨባጭ ማሸነፍ ከተቻለና የፖለቲካ ምህዳሩ ሰፊ ከሆነ በ ላ በዚያ አገር ላይ የፖለቲካ ትግል ማከኼድ ይቀርና በሌሎች ዴሞክራሲያዊ ባህል በዳበረባቸው አገሮች ንደሚደረገው በተለያዩ የአገሪቱ ፖለቲካዊ፤ ማህበራዊ ና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ክርክር ማካሄድ፤ ድርድር ማድረግና በምርጫ ግዜ ደግሞ ጠንከራ ተፎከከሪ ሆኖ ለማሸነፍ ጥረት አስፈላጊ ነው::

ወደ አገራችን ተጨባጭ ሁኔ ስንመለስ በአገራችን ተደራጅቶ ለመ ገል የሚያስችልና ህገ- መንግስ ዊ ድንጋጌ አለ፤ ነገር ግን ህገ -መንግስቱ ላይ በግልፅ የተቀመጡ መብቶቻችን ተግባራዊነት ላይ ችግሮች ያሉበት ቢሆንም ንኳን ሠላማዊ ትግልን ማካሄድ ትክክል ብቻ ሳይሆን አማራጭም አይኖረውም:: ይኼ ሁኔ ባለበት አገራችንም የትጥቅ ትግል ማካሄድ ህገ-ወጥ ተግባር ቢሆን አያስደንቅም:: ግን ይሄ ሁኔ ያለም ትጥቅ ትግል ማካሄድ ትክክል ነው ብለው ወደ ትግሉ ገባን ያሉ ሀይሎች መኖራቸው አልቀረም::

በዚህ አገር ላይ ከዚህ በ ች በምዘረዝራቸው ጉዳዮች ምክንያት ስለ ሰላማዊ ትግል አስፈላጊነትና ውጤቱም

አስተማማኝ መሆኑን ለማሳየት ሞክራለው:: በተቃራኒው የትጥቅ ትግልን ማካሄድ ምን ያህል ምክንያ ዊ ያልሆነና አፍራሽ የሆነ፤ በተጨማሪም የህዝቡን ዘላቂ ጥቅም የማያስጠብቅ ንደገናም በኢትዮጵያ ሪክ በተደጋጋሚ የተሰራውን የሥርዓት ለውጥን ሳይሆን መንግስ ዊ ለውጥን ብቻ ሳቢ ያደረገ ፖለቲካዊ ስህተትን መድገም ነው::

1ኛ/ ሠላማዊ ትግልን በአገሪቱ ውስጥ ማካሄድ ንደሚቻል ህገ-መንግስ ዊ ውቅና አለ:: ሠላማዊ ትግልን ለማካሄድ መንገዱ አልጋ በአልጋ ባይሆንም ሠላማዊ ትግል ለማድረግ የሚያስችሉ መንገዶች ግን ሙሉ በሙሉ ዝግ አልሆኑም:: ይህ ሁኔ ስካለ ድረስ የፖለቲካ ምህዳሩን ለማስፋት መ ገል ነው ንጅ የትጥቅ ትግልን ንደ ዋነኛ መፍትኄ አድርጎ ነው::

2ኛ/ በሀገራችን የተደረጉት ለውጦች ሁሉ ከሰላማዊ መንገድ ውጭ በመሆናቸው አንድም ግዜ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የገነባ አይደለም ለመገንባት ፍላጎትም ያሳየ መንግስትም ለማየት አል ደልንም:: ይልቁንም ገና ሥልጣኑን በተቆናጠጡ ማግስት ወሳኝ የሆኑ የሰው ልጅ መብቶችን በማፈን ነው የሚጠመዱት:: ከዚህ በተደጋጋሚ ከ የና ከ ወቀ ሀቅ ውጭ አሁን ምን አዲስ ነገር ተገኝቶ ነው የትጥቅ ትግል አማራጭ የሚሆነው:: በሆነ ተአምር ንኳን ቢሳካላቸው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በኢትዮጵያ ለማምጣ ቸው ምንም አይነት ዋስትናም ሆነ ማረጋገጫ አይገኝም::

በተጨማሪም አሁን ባለው የሀገራችን ውነ የብዙ ብሄር መገኛ፤የብዙ ሀይማኖቶች መኖርያ ንደ መሆናችንን ለሚያስተውል ርስ በርስ ጦርነትና በብጥብጥ ለውጥ አመጣለው ብሎ ማለት በ ሳት መጫወት ነው:: ንደው ኢህአፓና ግንቦት 7 ና ሌሎችም በጠመንጃ ሃይል ወደ ስልጣን ቢወጡ መልሰው ስልጣናቸውን በሠላማዊ ትግልስ ለማስረከባቸው የትኛው አዋቂ ነው ሊነግረን የሚችለው ወይንስ በምን ዓይነት የደም ምርመራ ነው ሊረጋገጥ የሚቻለው:: ስለዚህ ሌላ የተራዘመ የሠላማዊ ትግል ከማድረግ አሁን ያለውንና የተጀመረውን ትግል አጠናክሮ መቀጠሉ አማራጭ የለውም ማለት ነው::

3ኛ. የትጥቅ ትግል የሰው ህይወትና የሀገር ሀብትን የሚያወድም መሆኑ ንደተጠበቀ ሆኖ የውጭ ሃይሎችን በ60ቹ ንደነበረው አለም በሁለት ጎራ ካልተከፈለች በስተቀር ድጋፍም ሆነ ትብብር ለማግኘት የሚቻል አይደለም:: ስለዚህ የስልቱን አዋጭነት የበለጠ ጥያቄ ውስጥ ይከተዋል:: የጉዳዩ ባለቤት የሆነውም የኢትዮጵያ ህዝብ አሁን ያለውን አንጻራዊ ሰላም ማጣጣም በጀመረበት ሁኔ የጦርነትን አማራጭ የያዘን ሃይል ይቀላቀላል ማለት ስህተት ነው:: ነሱ በአሜሪካና በአውሮፓ በተንደላቀቀ ሁኔ የኖሩ በምስኪኖች ደም ቤተ-መንግስት ለመግባት ማሰብም ነውረኝነት ነው::

ህዝቡንም በሠላማዊ ትግሉ ተስፋ ንዲቆርጥና ነሱን ናፋቂ ንዲሆን ከማድረግ ውጭ የተለየ ፋይዳም አይኖረውም:: ጦርነትን መዋጋት ብቻ ሳይሆን መስራትም ንችላለን ለሚሉትና ለረዥም ዓመ ት በውጊያ የዳበረ ልምድ ላላቸው የወቅቱ ገዥዎቻችን የሚመችና አሸናፊ የሚያደርጋቸው አማራጭ ነው:: ይልቁንስ ነሱ የማይችሉት፤ የሚከብዳቸውና ተሸናፊ የሚያደርጋቸው ሠላማዊ የትግል ስልት ነው:: ምክንያቱም ዚህ ላይ የሚስተናገደው ሃሳብና የፖሊሲ አማራጭ በቻ በመሆኑ ነው::

ከነዚህ ምክንያቶች በመነሳት የሠላማዊ ትግል ተመራጭ ብቻ ሳይሆን ዋስትና የሚሰጥ የትግል ስልት ነው:: የትጥቅ ትግልን ንከተላለን የሚሉ ሃይሎች አብዛኞቹ ሰላማዊ ትግልን ያልሞከሩና ውስጡ ገብተው ያልፈተሹ ናቸው:: አንዳንዶቹ ደግሞ 97 ዓ.ም የመንግስት ስልጣን አልገኝ ሲል አኩርፈው የገቡ መሆናቸውን ለተመለከተ መነሻቸው ለህዝብ መቆርቆርና በዚህ ሀገር ዘላቂ የሆነ ዴሞክራሲያዊ ስርአት የመትከል ሳይሆን ጭፍን ጥላቻ መሆኑን ይገነዘባል::

የትጥቅ ትግል መፍትሄ ንደሚያመጣ የሚነግሩን አርበኞቻችን በዚህ 22 አመት ውስጥ አንድም የገጠር ቀበሌን ይዘናል ሲሉ አለመስማ ችን ሌላው ግርምትን የሚያጭር ነው:: አንዳንዴም ነሱስ ገብቶአቸው ይሆን? ንድል ገደዳለው:: ነዚህን ሃይሎች አሳምኖ ወደ ሰላማዊ ትግሉ ማስገባት አስቸጋሪ ነው:: ምክንያቱም የሰላማዊ ትግሉ አላማ ሳይገባቸው ቀርቶ ሳይሆን በውስጣቸው ስር የሰደደው የግራ ፖለቲካ አስተሳሰብ ስለሚያስገድዳቸው ና በ60ቹ የተሸነፉበትን የፖለቲከ

ቁማር የዞረ ድምረ ሂሳብ ለማወራረድ ካላቸው ፍላጎት የመነጨም ነው፡፡

የትጥቅ ትግል የሚያራምዱትን ሃይሎች ብዙ ጉድለትና ክፍተት ባለበት የኢህአዴግ አገዛዝ ቀርቶ የተሳከ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በዘረጋ ሥርዓትም ሠላማዊ ማድረግ በጣም ከባድ ነው፡፡ ገዥውን ፓርቲ ነደ ሀገር አፍራሽና ወራሪ ሃይል ለሚቆጥሩ ወገኖች ሰላማዊ ትግሉ ውስጥ ተሳትፎ ማድረግ ንደ ፈሪንትና ከሀዲነት የሚያስቆጥር ተግባር ነው፡፡ ስለዚህ ነሱ የሚመርጡት ነሱን በአቋራጭ ስልጣን ላይ ቁብ ሊያደርግ የሚችል የሀገር ውስጥ ብጥብጥና ትርምስ ስኪፈጠር መጠበቅ ነው፡፡ ስለዚህ የትጥቅ ትግል ያደረግን ነው በሚል የማይጨበጥ ነገር ያወሩ አጋጣሚውን መጠባበቅ ነው፡፡

የሰላማዊ ትግልን አላስፈላጊነት ለማስረዳት የሚያቀርቡት ምክንያትም በጠመንጃ የወጣ ሃይል በጠመንጃ ብቻ ነው የሚወርደው የሚል ነው፡፡ በመጀመርያ በነጻና ፍትሀዊ ምርጫ ኢህአዴግ ስልጣኑን የሚለቅ መንግስት ቢሆን ኖሮ ንኳን ግንቦት 7 ና ኢህአፓ ዚህም ሀገር ያለን በሰላማዊ ትግል የምን ገል ፓርቲችም ትግል ባላስፈለገን ነበር፡፡

ኛም የምናደርግ የነበረው በምርጫ ፋክክር ስልጣን ለማያዝ ዝግጅት ማድረግ ነው፡፡ በጠመንጃ ስልጣን የያዘ ሃይል በሰላማዊ መንገድ ስልጣኑን ሊለቅ ካልቻለ አሁን የትጥቅ ትግል የሚያደርገው ሃይልም በተመሳሳይ ስልጣኑን በሰላማዊ መንገድ አይለቅም ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም ዛሬ ላይ የሰራ ሎጅክ ነገም ይሰራል፡፡ በትጥቅ ትግል ለስልጣን የበቃ ሀይል በሰላማዊ መንገድ ንደሚለቅ ርግጠኛ መሆን የማይቻል ከሆነ በትጥቅ ትግል ውጤት አመጣለው ማለት ስህተት ነው፡፡

በረዥም ጦርነት አዲስ ሀይል ስልጣን ይዞ በሠላማዊ በሆነ መንገድ ንደ አዲስ ትግል ከመጀመር ይልቅ አሁን ያለውን ገዢ መንግስት ኢህአዴግ በ ሠላማዊ ትግል ለመለወጥ ጥረት ማድረግ አንደሚሻል የዜሮ ድምር ፖለቲከኛ ካልተሆነ በቀር ቀላል የሂሳብ ስሌት ነው፡፡

በመጨረሻም ለሀገራችን የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት ግንባ ባህል መዳበር ና መጎልበት ወሳኝ የሆኑ ባለድርሻ አካላት ሊወጡት ይገባቸዋል የምለውን ሃሳብ ጠቁሜ ጽሁፌን ልቀጭ፡፡

1ኛ/ ገዥው ፓርቲ ኢህአዴግ ተገቢውን የመሪነት ሚና በአግባቡ መወጣት አለበት፡፡ ተቃዋሚችን ባልሆነ ነገር ማዋከቡን ትቶ ለዚች ሀገር ገንቢ ሚና ሊጫወቱ ንደሚችሉ ተገንዝቦ ተገቢውን አክበሮትና ውቅና ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ላለመግባባት በር የሚከፍቱ አሰራሮችን መፈተሽና ማስተካከል ይኖርበ ል፡፡ ያለመግባባት ችግርም ተፈጥሮ ሲገኝ በድርድር ለመፍ ት ዝግጁ መሆን አለበት፡፡

በአንጻሩም ክርችም አድርጎ የዘጋውንና ለብቻው በሞኖፖል የያዘውን ሚዲያንና የምርጫ ቦርድን ሁሉንም ኩል ተጠቃሚ በሚያደርግ መልኩ ማደራጀት አስፈላጊ ነው፡፡ ለምክክር ና ለድርድርም ሆደ ሰፊ መሆን አለበት፡፡ አገር ያወቀውን ጸሃይ የሞቀውን ግልጽ የሆኑትን ድክመቶቹን ለይስሙላ ሳይሆን ከልብ አምኖ ማስተከከል ይኖርበ ል፡፡ ግልጽ ፍትሃዊ ና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ተካሂዶ ህዝብ በካርዱ የማይፈልገውን ከሥልጣን የሚያወርድበት የሚፈልገውን ወደ ስልጣን የሚያወጣበት ሥርዓት ለመፍጠር ካልሰራ ከ ሪክ ተጠያቂነት አይድንም፡፡

2ኛ/ የትጥቅ ትግል ናካሂዳለን የሚሉም ሆኑ በሁለገብ ትግል የሚነቀሳቀሱ ሃይሎች አውሮፓና አሜሪካ ቁጭ ብለው በሚልኩት ዶላር ሀገር ተበጥብጦ ቤተ-መንግስት ንገባለን የሚለውን ቅዠት አቁመው፤ በደሀ የገበሬ ልጅ ደም ሥልጣን ላይ ንወጣለን ማለት የሚያሳፍር ተግባር ንደሆነ ተገንዝበው፤ 21ኛው ክፍለ ዘመንን የማይመጥን ስልት መሆኑን ተረድተው የበለጠ ኢህአዴግ ተጠቃሚና አሸናፊ ከሚያደርገው ስልት በመውጣት ከ ሪክ ተጠያቂነት ራሳቸውን ሊያድኑ ይገባል፡፡

በአንጻሩም አገር ውስጥ ሆነው ሰላማዊ ትግሉን በመምራት ውድ ዋጋ በመክፈል የመንግስት ለውጥ ሳይሆን የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት ለቀጣዩም ትውልድ ዋስትና የሚሰጥ ልህ አስጨራሽ ትግል ለሚያደርጉት ግልጽ

አላማና ግብ ሳነገቡ ፓርቲች  ንቅፋት ከመሆን ድርጊ  ቸው ሊ  ቀቡ ይገባል፡፡

3ኛ/ ህዝቡ የትጥቅ ትግል የመንግስትን  ንጂ የሥርዓት ለውጥ  ንደማያመጣ ተረድቶ፤ የሰው ህይወትንና የአገር ሃብትን የሚያወድም መሆኑን ተገንዝቦ፤ በነሱ ላይ ያለውን ተስፋ ከወዲሁ መፋቅ አለበት፡፡ ይልቁንስ ዘላቂ የሆነ የሥርዓት ለውጥ ሊያመጣ የሚችለውንና ዋስትና የሚሰጠውን የሰላማዊ ትግልን ተደራጅቶ በቁርጠኝነት መደገፍ አለበት፡፡ በሰላማዊ ትግሉ ማነው የማይናወጥ አቋም ያለው የሚለውን ፓርቲ በቅርብ በመፈተሽ ከጥላቻ በጸዳ መልኩ በምክንያ  ዊነት ላይ ተመስርቶ ትግሉን መቀላቀል አለበት፡፡

ከስሜ  ዊነት ተላቆ በስክነት ጉዳዮችን በመመርመር ለአገሪቱ መጻኢ  ድል፤ለቀጣዩ ትውልድ  ጣ ፈን የሚጨነቁ፤ ለሥልጣን ሳይሆን ለዴሞክራስያዊ ሥርዓት ግንባ  የበኩላቸውን  የተወጡ ላሉት፤ ለመደማመጥ፤ ለመቻቻል፤ ለመግባባት፤ ለስላም  ና አብሮ ለመስራት የቆረጡትን በመለየት በምርጫ ሰዓት ድምጽ በመስጠት የሰለጠነና የነቃ ህዝብ መሆኑን በተግባር በማረጋገጥ  ሪካዊ ግዴ  ውን መወጣት ይኖርበ  ል፡፡

4ኛ/ ተቃዋሚዎች በአፋችን ዘወትር የምንናገረውን ያህል የሠላማዊ ትግል ጠበቆች ነን ማለት አያስደፍርም፤ ለዚህም ማረጋገጫ የሚሆነው አንዳንድ የተቃዋሚ አመራሮች ትጥቅ ትግል የሚያደርጉትን ሃይሎች ተገደው እንደገቡበት አድርገው ሲናገሩ መሰማታቸው ነው፡፡  ሰላማዊ ትግል ላይ ያለን አቀም ግልጽ  ና የጠራ መሆን አለበት፡፡

ስለዚህ ወለም ዘለም ማለተችንን ትተን በግልጽ ለሰላማዊ ትግል ዘብ መሆናችንን ማሳየት አለብን፡፡ በሰላማዊ ትግሉ ህዝቡን አስተባብረን ለውጤት  ንድንበቃ ካስፈለገ ግልጽ መል ክት በትጥቅ ትግል ስም ለሥልጣን ለሚሯሯጡት ማስተላለፍ አለብን፡፡ ተቃውሞአችንን በአደባባይ ማሰማትም አለብን፡፡  ንደ ምስጥ ውስጥ ውስጡን  የበላ በመጨረሻ ከሚያጠፋን ይሄን ብናገር ምን ልባል  ችላለው ከሚል የ ወደድ ባይነት ፖለቲካ  መውጣት ያስፈልጋል፡፡  ያለበለዚያ የምንፈልገውን ለውጥ ሳናመጣ ጀንበር በላያችን ትጠልቃለች፡፡

በሌላም በኩል ለመደማመጥ ለመከባበር ለመግባባት ከመንግስት ጋር ብቻ ሳይሆን  ርስ በርስ ግንኙነትም ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡ በፓርቲው የጋራ አቋም ላይ የማይናወጡ ስሜ  ዊ ያልሆኑ ጠንከራ አባላቶችን ለማፍራት መሰረተ ሰፊ ስራ መስራት ይኖርበ  ል፡፡ ለመፍረሳቸው ሆነ ለመድከማቸው ኢህአዴግን ተጠያቂ ማድረግ ብቻ ሳይሆን  ራሳቸውንም ለመፈተሽ ዝግጁ መሆን አለባቸው፡፡ ለፕሮግራማቸውና ለመተዳደርያ ደንባቸው ተገዥ መሆንንና ገዥው ፓርቲም ከሥልጣን የመውረድንና የመውጣትን ዴሞክራሲያዊ ባህል በማጎልበት ተቃዋሚ መሆንን  መለማመድ ይኖርበ  ል፡፡

ከአዳነ ታደሰ
የኢዲፓ የፋይናንስ ዘርፍ ኃላፊ